# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 53 ግንቦት 13 2001 ዓ.ም


ከመከላከያ ሠራዊት፣ ከፖሊስና ከአንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ እየታደኑ ያሉት ሰዎች ሲታይ ወንጀላቸው የዘውግ ማንነታቸው እንደሆነና እስራቱና እንግልቱም ይህንኑ መሠረት ያደረገ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ሆኗል። ይህም እጅግ አደገኛ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ ግንቦት 7 በተደጋጋሚ መግለጫ አውጥቷል። በተለይ የብአዴን አባላት ቆመንለታል የሚሉትን ህዝብ በዘውግ ማንነቱ የጥቃት ሰለባ ሲሆን ማየት እጅግ አሳፋሪና አዋራጅ ድርጊት መሆኑን ተገንዝበው "እሽክርና በቃኝ ወግድልኝ" የማለት ድፍረት እንዲኖራቸው በመግለጫው አሳስቧል።

የግንቦት 7 እርሰ አንቀጽ

## የግንቦት7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ የአውሮፓ ጉብኝታቸውን እንደቀጠሉ ነው፣ ለ2 ተከታታይ ቀናት ከአውሮጳ ህብረት ባለሥልጣናት ጋር ተወያዩ

የግንቦት7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ የአውሮፓ ጉብኝታቸውን እንደቀጠሉ ነው:: ከትናንትና በስትያ ማክሰኞ ግንቦት 11 ጀምሮ ለ2 ተከታታይ ቀናት ከአውሮጳ ህብረት ባለሥልጣናት ጋር ተገናኝተው በኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ ጉዳዮች ላይ መወያየታቸው ተገለጸ

የግንቦት 7 ለፍትህ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ በኢትዮጵያ አገራችን እውነተኛ ዲሞክራስ እንዲሰፍን ያለውን ቁርጠኝነት ለምእራባዊያን ወዳጅ መንግሥታት ለማሳወቅና ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ለሚደረገው ሁለገብ ትግል የፋይናንስ፣ የፖለቲካና የሞራል ድጋፍ በየአገሩ ተበታትኖ ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ለማሰባሰብ በአውሮጳ ጉብኝት የጀመሩት የንቅናቄው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የአውሮፓ ህብረት ዋና መቀመጫ በሆነው ብራሰልስ ከተማ በመገኘት ከአውሮጳ ኮሚሽንና የአውሮጳ ካውንስል ባለስልጣናት ጋር እንደተወያዩ ከንቅናቄው የውጭ ግንኙነት ክፍል የደረሰን ዜና አረጋግጦአል ::

ዶ/ር ብርሃኑ ከባለስልጣኖቹ ጋር ውይይት ባደረጉበት ወቅት እንደዋና ነጥብ ያነሱት የህብረቱ አባል መንግስታትም ሆኑ ህብረቱ በምርጫ 97 ወቅት ህዝባችን በመረጠው ህዝብ ለመተዳደር ያሳየውን ቁርጠኝነትና የሰጠውን ህዝበ ውሳኔ በመለስ የሚመራው አምባገነን አገዛዝ በሃይል ሲቀለብስ ዝም ብሎ በመመልከታቸው ኢትዮጵያዊያን በአንድ ወቅት ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር በአገራቸው ሊመጣ ይችላል ብለው ሰንቀውት የነበረው ተስፋ እንደሚሸሸና በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ድጋፍ ጭምር በአገራቸው የሰለጠነ ፖለቲካ ይካሄዳል ብለው ማሰባቸው እንደሃጥያት ተቆጥሮ "እስኪ የሚያድናችሁን የውጭ ሃይል እናያለን" በሚል እብሪት በመለስ ዜናዊ ኋላ ቀር ዘረኝነት እጅ በገዛ አገራቸው ተዋርድውና ሽንፈትን ተቀብለው እንዲኖሩ እንደተፈረደባቸው አስረድተዋል ::

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በድርጅቱ ውስጥና ውጭ የተደናገጠው ወያኔ ቀደም ሲል ሥራቸውን የለቀቁ ፖሊሶች ታድነው እንዲያዙ መመሪያ አንዳስተላለፈ ተደረሰበት

ሰሞኑን በተፈጠረበት መደናገጥ የተነሳ መያዣ መጨበጫ ያጣው የወያኔ አገዛዝ፣ ስራቸውን በተለያዩ ምክንያቶች የለቀቁ የፖሊስ አባላት እየታደኑ እንዲያዙ ትእዛዝ ማስተላለፉን የፖሊስ ምንጮቻችን ገለጹ። ከአዲስ አበባ የግንቦት 7 ዘጋቢ የተላከው ዜና እንደሚያመለክተው የወያኔን ስርአት ሲያገለግሉ የነበሩና በስርአቱ ደስተኛ ባለመሆን ስራቸውን የለቀቁ የፖሊስ አባላት ታድነው እንዲያዙ ትእዛዝ የተላለፈው ከፖሊስ ኮሚሽነሩ፣ ከወርቅነህ ገበየሁ ሲሆን፣ በተለያዩ የወረዳና የቀበሌ ጽህፈት ቤቶች የሚሰሩ የደህንነት ሀይሎች ትእዛዙን እንዲአስፈጽሙ አስፈላጊውን መረባረብ እንዲያደርጉ ያዛል።

ከግንቦት 7፣ 1997 ምርጫ በሁዋላ በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት ስራቸውን በፈቃዳቸው እየለቀቁ ስርአቱን ወደሚቃወሙ ሀይሎች በስፋት እየጎረፉ በመምጣታቸው በእጅጉ የተደናገጠው የመለስ ቡድን፣ ይህን ቀጭን ትእዛዝ ለማውጣት መገደዱን ምንጮቻችን ጠቁመዋል።በርካታ የፌደራል ፖሊስ አባላት፣ የግንቦቱን ምርጫ ውጤት በመቃወም ሰልፍ የወጡ የአዲስ አበባ ወጣቶችን አንገድልም በማለታቸው መባረራቸው በወቅቱ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን መዘገቡ የሚታወስ ሲሆን፣ እነዚህ የተባረሩ ፖሊሶች በተለያዩ የተቃዋሚ ድርጅቶች በመቀላቀል ስርአቱን በመፋለም ላይ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## መለስ ዜናዊ አፊሪካ ኮንፊደንሻል ለተባለ ጋዜጣ በሰጠው ቃለመጠይቅ የግንቦት 7 ንቅናቄ ራስምታት እንደፈጠረበት አመነ

ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ ግንቦት ሰባት በከፍተኛ ሁኔታ እያወከው እንደሆነ ተናገረ። መለስ ዜናዊ ግንቦት ሰባት የጎን ውጋት እንደሆነበት ያመነው አፍሪካ ኮንፊደንሻል ከተባለ ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቃለምልልስ መሆኑ ታውቋል።ጋዜጣው "ግንቦት ሰባት የተባለው ንቅናቄ ለስልጣንህ ያሰጋሓል ?" ብሎ መለስን ለጠየቀው ጥያቄ እንደሌላ ጊዜ ሳይሸፋፍን ግንቦት ሰባት የለቀቀበትን ፍርሀት በግልጽ መናገሩ በወያኔ ሰፈር እንደቋያ እሳት እየተቀጣጠለ ለሄደው ሽብር አይነተኛ አብነት መሆኑ ተመልክቷል።

አፍሪካ ኮንፊደንሻል ወያኔ ስልጣን ላይ ለረጅም አመት የቆየ ድርጅት መሆኑን ጠቅሶ "ስልጣን ላይ የቆያችሁት በራሳችሁ ጥንካሬ ነው ወይስ በተቋዋሚ ድክመት ነው?" ብሎ ላቀረበለት ጥያቄ መለስ ዜናዊ የተለመደ ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ አይነት መልስ ሰጥቷል።እፍረት ብሎ ነገር ያልፈጠረበት መለስ በሲዊድን ሶሻል ዴሞክራሲ ፓርቲ ለ80 አመት ፤በእንግሊዝ ደግሞ ሌበር ፓርቲ ከሁለተኛ አለም ጦርነት ጀምሮ እየገዙ ነው፤የእኛ አስራ ስምንት አመት መግዛት ምንድ ነው የሚገርመው ብሎአል። እንደታዛቢዎች የወያኔው ቁንጮ የኢትዮጵያን ህዝብን ለዘመናት ረግጦ ለመግዛት ያለውን ምኞት እንደቀደመው ጊዜው ሁሉ ዛሬም ይፋ ማድረጉ ያስተላለፈው ግልጽ መልእክት አለ። እሱም የኢትዮጵያ ህዝብ በሀገሬ ሳልፈራ እና ሳልሸማቀቀ ተከብሬ እንደ ሰው መኖር አለብኝ፤ የራሴን እና የቤተሰቤን ህልውና እና እድል ፈንታ ለቀማኛ አሳልፌ መስጠት ይበቃኛል ብሎ ነውረኛውን የወያኔ አገዛዝ አምርሮ ካልታገለ፤ የመለስ ብድን የኢትዮጵያን ህዝብ ለዘመናት ረግጦ ለመግዛት ማስማማቱን ቀጥሎበታል ተብሎአል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## በአማራው ክልል በርካታ ሰዎች የግንቦት 7 አባላት ናችሁ እየተባሉ በመታሰር ላይ ናቸው

ከአማራ ክልል የሚደረሰን ዜና እንደሚያመለከተው፣ የወያኔ አገዛዝ በርካታ የሰራዊት አባላትንና ወጣቶችን የግንቦት 7 አላማን ታራምዳላችሁ በሚል ሰበብ በተለያዩ የወረዳ እስር ቤቶች እያጎረ ይገኛል። በጎጃም ዞን በይልማና ዴናሳ ወረዳ መላኩ በለው የተባለ ታጠቂ የግንቦት 7ትን የሽፍታ ቡድን ታደራጃለህ ተብሎ መታሰሩን ዘጋቢያችን የገለጸ ሲሆን፤ በባህርዳር፣ በደጀን፣ በደብረማርቆስ፣ በእብናት፣ በወረታና በደብረታቦር ከተሞች በርካታ የብአዴን አባላትና ወጣቶች በገፍ በመታሰር ላይ ናቸው።

ወያኔ በእነዚህና በሌሎች ከተሞች የስለላ መረብ መዘርጋቱን የተናገሩት ዘጋቢዎቻችን፣ በፊት ቅንጅትን ሲመሩና ሲደግፉ የነበሩት ሰዎች አሁን ደግሞ ከግንቦት 7 ጋር በተያያዘ በመታሰር ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል። በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ወረዳዎች ያሉ እስርቤቶች መሙላታቸውን ከተለያዩ ከተሞች የሚደርሱን መረጃዎች የሚያመለክቱ ሲሆን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ "ወያኔ ልትወድቅ ስለሆነ መዋጮ አትክፈሉ" የሚል ቅስቀሳ በስፋት እየተሰማ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። አምባገነኑና ዘረኛው መለስ ዜናዊ በክልሉ ህዝብ ሁኔታ እየተደናገጠ በመምጣቱ ሰሞኑን በክልሉ ጉብኝት ያደረገ ቢሆንም፣ ህዝቡ ግን አሁንም በአገዛዙ መማረሩን ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘ ዜና፥ የግንቦት ሰባት ጋዜጠኛ ከአዲስ አበባ ያደረሰን ዘገባ እንደሚያመለክተው፣ "በግንቦት ሰባት የተመራ መፈንቅለ መንግስት ሊካሄድ ሲል ደርሼ አከሸፍኩ" ካለበት ማግስት ጀምሮ፣ ወያኔ ከተለያዩ መስሪያ ቤቶችና ከብአዴን ውስጥ በርካታ ካድሬዎችን እያደነ በማሰር ላይ እንዳለ ዘግቧል።

በተጨማሪም የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ሲቪል ሰራተኞችና በርካታ የፖሊስ አባላትና ወታደሮችም እየታሰሩ መሆናቸው ታውቋል። እንደዘጋቢያችን ከሆነ የታሰሩ ሰዎች ቁጥር በመቶዎች የሚቆጠር ሲሆን፣ በርካታ ዜጎች የገቡበት እየጠፋ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ በተለይ በግምገማ ስም ነባር የብአዴን ካድሬዎችን ለመመንጠር የሚያስችለው ቅድመ ዝግጅት መጠናቀቁን ከደህንነትና ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ አካባቢ የተገኙ መረጃዎችን ጠቅሶ ሪፖርተራችን ከአዲስ አበባ ዘግቧል። በተለይ ከብአዴን አባላት ጋር ለሚደረው ግምገማ ይረዳ ዘንድ፣ በርካታ ሰነዶች መዘጋጀታቸውንና ከነዚህም ሰነዶች መሃከል የአማራው ብሄር ትምክተኝነት በሚል የተዘጋጀው ጽሁፍ እንደሚገኝበት ለማወቅ ተችሏል። በዶክመንቶቹ ውስጥ እንደሰፈረው አሁን በበአዴን ካድሬዎች ውስጥ እየተብላላ የመጣው "የአንድ ብሄር የበላይነት ይቁም" የሚለው ጥያቄ ከአማራ ትምክህተኝነት የሚመነጭ ነው ተብሎ እንደተጻፈ ለማወቅ ተችሏል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ጊዜው ሀቅን የመጋፈጥ ድፍረት ይጠይቃል!

ወያኔ "በግንቦት 7 ንቅናቄ የተመራን የመንግሥት ግልበጣ አከሸፍኩ" በማለት ዓለምን ባስደመመበት ዕለት "ከመፈንቅለ መንግስቱ" ሙከራ ጋር በተያያዘ ሰላሳ አምስት ሰዎች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስታውቋል። ሌሎችም የሚፈልጋቸው እንዳሉም ገልጿል። ሊታሰሩ ከሚፈለጉ ሰዎች መካከል የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ከመደረጉ ከወራት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሰዎች መኖራቸውን ዓለም በአግራሞት እየሰማ ነው።

በዚህም በአንድ በኩል የነ መለስ ፍርሃት ደረጃ በሌላ በኩል ደግሞ የህዝቡ ተቃውሞ ውስጥ ውስጡን እየሰደደ ሄዶ የነመለስ ጎጆ ከመሰረቷ መንደድ መጀመሯንና የግንቦት 7 ንቅናቄም ወያኔን የሚያቃዠው ሀይል እንደሆነ ዓለም አስተውሏል። በተለይ የነ መለስ "ጠንካራ መንግስት ነኝ" ቱልቱላ የእምቧይ ካብ እንደሆነ ደጋፊ መንግስቶቻቸው በሚገባ ልብ እንዲሉ አድርጓቸዋል። እነርሱንም ከተኙበት አባንኗቸዋል። በአፍሪካ ቀንድ አለን በሚሉት ጥቅም ምክንያት ወያኔ ሰላምና መረጋጋትን መፍጠር እስከቻለ ድረስ የሚኮራበት ሽሪክም ባይሆን አብሮ መሥራት ይቻላል ከሚል ፍልስፍና ለዘመናት ኢትዮጵያውያን በብዙ ሰልፍና እሮሮ ያሰሙትን የሙብት ጩሀት ላለመስማት "ጆሮ ዳባ ልበስ ብለው" በራቸውን ከርቸም አድርገው የኖሩ ምዕራባውያን አካሄዳቸው ለአገሪቱም ሆነ ለዘላቂ ጥቅማቸው አዋጭ እንዳልሆነ ለመገንዘብ ችለዋል።

በሰሞኑ መደናገጥ እስከ አሁን ያፈናቸውን፣ ያሰራቸውንና የገደላቸውን ሰዎች ቁጥር ወያኔ ይፋ ባያደርግም ገና የሚያድናቸው ሰዎች እንዳሉ ግን አልሸሸገም። እንዲያውም "እገሌንና ኤገሊትን ያያችሁ ጠቁሙኝና ወሮታውን እከፍላለሁም" እያለ በቴሌቪዥንና በራድዮ በየቀኑ ቢማጸንም ህዝቡ ግን "ጎሽ፣ ደግ፣ አደርገው ነው!" እያለው ነው። ምንም እንኳ የተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ወደ አርባ አንድ የሚጠጉ ሰዎች ታስረዋል ቢሉም ለግንቦት 7 እየደረሰ ያለው መረጃ ግን እየታደኑ የሚታፈሱ ሰዎች ቁጥር በእጅጉ እንደሚበልጥና በብዙ መቶዎች የሚቆጠር ሊሆን እንደሚችል እያሳየ ነው።

በተለይ ከመከላከያ ሠራዊት፣ ከፖሊስና ከአንዳንድ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መሥሪያ ቤቶች ውስጥ እየታደኑ ያሉት ሰዎች ሲታይ ወንጀላቸው የዘውግ ማንነታቸው እንደሆነና እስራቱና እንግልቱም ይህንኑ መሠረት ያደረገ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ሆኗል። ይህም እጅግ አደገኛ እንደሆነ በማያሻማ ሁኔታ በመግለጽ ግንቦት 7 በተደጋጋሚ መግለጫ አውጥቷል። በተለይ የብአዴን አባላት ቆመንለታል የሚሉትን ህዝብ በዘውግ ማንነቱ የጥቃት ሰለባ ሲሆን ማየት እጅግ አሳፋሪና አዋራጅ ድርጊት መሆኑን ተገንዝበው "እሽክርና በቃኝ ወግድልኝ" የማለት ድፍረት እንዲኖራቸው በመግለጫው አሳስቧል።

በዚህ ሳያበቃ የግንቦት 7 በመግለጫው በተለይ ኢትዮጵያንና ህዝቧን የሚወዱ በስማቸው የሚነገድባቸው የትግራይ ዘውግ አባላት ይህን እኩይና ብካይ ድርጊት ለእነርሱም ሆነ በዘመናት ለኢትዮጵያ አንድነት ሲዋደቅና ሲደማ ለነበረ ለጀግናው የትግራይ ህዝብ የማይበጅ፣ አብሮ ለዘመናት ደግና ክፉን እየተካፈለ በኖረ ህዝብ መካከል ቁርሾንና ቂም በቀልን ጥሎ የሚያልፍ፣ በታሪክም የሚያስጠይቅ እንደሆነ ተገንዝበው የነ መለስንና የተከታዮቻቸውን መሰሪ ግብር እንዲያስቆሙ ጥሪ አድርጓል።

ኢትዮጵያችን የሁላችንም ነች። አገራችን ከኛ ከዜጎቿ የሚተርፍ እጅግ የተትረፈረፈ እምቅ ሃብት የያዘች ለሀገር ጥቅም የሚቆረቆር፣ የዜጎቿን እምነት ያገኘ መንግስት ብታገኝ ዛሬ የአለም መሳለቂያ ካደረጋትና ዜጎቿን ካሸማቀቀ ድህነት ለመገላገል የምትችል ድንቅ አገር ነች። ያች ሀገር አንድ ዜጋ ከሌላው ዜጋ፣ አንድ ዘውግ ከሌላው ዘውግ የበታች የማይሆንባት የማድረግ ሃላፊነት የሁላችንም ነው እንላለን።

ዛሬ ያለችው ኢትዮጵያ እጅግ አዋራጅ ነች። በአንድ ሀገር ውስጥ አንዱ የበላይ ሌላው የበታች እንዲሆን የተደረገች። ከአንድ ዘውግ የተወጣጡ አለአግባብ ባገኙት ጥቅም ተቧድነው ሁላችሁንም አዋርደን በባርነት እንገዛችኋለን የሚሉባት። ይህ ደግሞ ለማንም እፎይታንና ሰላምን ሰጥቶ አያኖርም። የአንድ ዘውግ የበላይነት በነገሠበት፣ ሌሎች ባርነት በሚሰማቸውና ተሸማቀው በሚኖሩባት ሀገር የሚዋረዱት የበታች እንዲሆኑ የተደረጉት ብቻ ሳይሆኑ በስሙ የተነገደበትና የበላይ የመሆን ቅዠት ያላቸው የተገኙበትም ዘውግ አባላት ሁሉ ናቸው ብለን እናምናለን። ውሎ አድሮ የሚያስከፍለው ዋጋ ለሁሉም አይበጅምና።

ከዚህ ውርደት ለመዳን የሚደረገው ትግል የሁላችንንም እውነትን የመጋፈጥ ድፍረት ይጠይቃል። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያንና ህዝቡን የምትወዱ የትግራይ ዘውግ አባላት ሁሉ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለውን ነባራዊ እውነታ የመጋፈጥ ድፍረት የምትላበሱበት፣ አድሎንና ጭቆናን በማንም ላይ ሲጫን ማየት የማትሹ፣ ያንን አደርጋለሁ የሚል እንደ መለስ ዓይነት ብካይ ቢገኝ መተኪያ የማይገኝለትን ውድ ህይወታችሁንም እንኳ ቢሆን ሰውታችሁ ለማስወገድ የማታቅማሙ እንደሆናችሁ የምታሳዩበት ሰዓት እነኋት እንላለን።



የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

# የማያድግ ጥጃ አንገቱ ይረዝማል::
## (ኢኮኖሚያችንና የኑሯችን አንዳንድ ምልከታዎች)

ታዛቢው ከአዲስ አበባ

አለማችን በፋይናንስና ኢኮኖሚ ማእበል ውስጥ ስትማስንና ከበርቴ መንግስታት ታይቶ ባልታወቀ ርብርቦሽ ኢኮኖሚያቸውንና ህዝባቸውን ከመከራና ስራ አጥነት ለመታደግ ሲጥሩ ይታያል:: ይህን መሳይ የመንግስታት ጥረት ለማየት በማይታሰብባት የዛሬይቱ ኢትዮጵያውያ ግን የስራ አጥነትና የዋጋ ግሽበት ህዝቡን እያሰቃዩት ይገኛሉ::

በቅርቡ ከአንድ ወዳጄ ጋር ሆኜ ቡና እየጠጣን ስንጨዋወት ሳለን ከተቀመጥንበት የካፌ በረንዳ የምንመለከተው ትራፊክ በአንዴ ውጥንቅጡ ወጣ:: መስቀለኛ መንገዱ ተሽከርካሪዎችን ማስተናበሩን እንዳይችል ተዘግቶ መኪናዎች መንቀሳቀስ አልቻሉም:: አሽከርካሪዎች ንዴታቸውን ጡሩምባቸውን ከመጠን በላይ በመንፋት ቦታውን የጨረባ ተዝካር አስመሰሉት::

ታዲያ ወዳጄን ኑሮ እንዴት ነው ብዬ ብጠይቀው ትንሽ አሰብ አድርጎ በተለመደው የምሰጥ ንግግሩ "ኑሮ ልክ እንደ ኢኮኖሚያችን የአዲስ አበባ ትራፊክን ይመስላኛል" አለኝ:: እንዴት ብለው "ሁለቱም ውጥንቅጥ ውስጥ ተዘፍቀው የያዙት አካሄድ ትርፉ ችግርና አሰልቺ ጥሩምባ ነው" ነበር አጭር መልሱ:: መልሱ ንፅፅራዊ ተመሳሳይነታቸውን በቅጡ እንድቃኘው አደረገኝ::

በአዲስ አበባችን በየቀኑ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በእንቅስቃሴ ላይ ናቸው:: የእንቅስቃሴያቸው ምክንያት እንደግለሰቡ ይለያይ ይሆናል እንጂ ግባቸው ግን ዞሮ ዞሮ ህይወትን ማሸነፍና ከተሳካም ማሻሻል ነው:: በመሰረቱ ስርዓት ያለው የትራፊክ አገልግሎት ተሽከርካሪዎች ቀልጣፋ የትራፊክ ፍሰትን በማስተናገድ አሽከርካሪዎችም ሆኑ እግረኞች የሚያደርጉትን የእለታዊ የኑሮ እንቅስቃሴ ለማፍጠንና ለማቀላጠፍ ከፍተኛ እርዳታን ያደርጋል:: ይህንን ስርአት ለማግኘት ግን ብዙ ነገሮችን ማቀናጀት የግድ ይሆናል:: መኪኖች: መንገዶች: ትራፊክ መብራት: የመኪና ጥገና: የነዳጅ አግልግሎት ወዘተ...አስፈላጊ ቢሆኑም ዋንኛውና ቅድመት የሚሰጠው ግን የትራፊክ ህግ ነው:: ይህ ህግ በቅጡ ተዘጋጅቶና ለመተግበር አመቺ በሆነ መልኩ ተቀርጾ ካልተገበረ ውጤቱ ብክነት: አደጋ: ስንክልና እና በአዲስ አበባችን እንደምናስተውለው ጆሮን አደንዛዥ ጥሩምባ ነው:: በመኪና ጥሩምባ ንዴቱን የሚገልጸው አሽከርካሪም ሆነ እኔ ልቅደም እያለ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋና ስቃይ የሚያስከትለው ግለሰብ የግዜና የገንዘብ ብክነት ሰለባዎችም ተሳታፊዎችም ናቸው:: መፍትሔያቸውም ዞሮ ዞሮ የትራፊክ ህጉና አተገባበሩ ዘንድ ነው:: ህጉ በጉልበተኞችና ከህግ በላይ ነን ባሉ ቡድኖች ያለተጠያቂነት እስከተሰበረ ድረስ የትራፊክ ፍሰት መታወኩ አይቀሬ ነው::

እያንዳንዳችን የእለት ህይወታችንን ለማሸነፍ ከወዲያ ወዲህ እንማስናለን:: ግባችንን ለማግኘት የግል ጥረታችን ትልቅ ሚና ቢኖረውም ህግ ፍቺዋን ባጣችበት አዲስ አበባ በጥረትና በወዝ ኑሮን ማሸነፍ አስቸጋሪ ከመሆን አልፎ የማይሞከር እየሆነ ነው:: በወዛችን ለማደር የምንጓዝበት መንገዶች በአብዛኛው የቀይ መብራት በዘላቂነት ይዟቸዋል:: ቀዩ መብራት በድንገት አረንጓዴ ሆኖ ወስላቶችና ወሮበሎችን አስተናግዶ ሌላው መንቀሳቀስ ሳይችል በቅጽበት እንደገና ወደ ተለመደው ዝግ መስመርነት ይለወጣል:: ብዙሃኑ በጭንቅንቅ መንገድ ላይ ሲዳክር እራሱንም ቤተሰቡንም የድህነት ሰለባ ያደርጋቸዋል:: በዚህ ህግ የለሽ ስርዓት ውስጥ ህዝቡ ከችግር ወደ ችጋር ሲያዘቀዝቅ የተወሰኑ ወሮ-በሎችና ግብረ አበሮቻቸው ግን በንዋይ ናውጠዋል:: ከህዝቡ እየጋጡ ግንብ: የህዝብ ካዝና እየዘረገፉ ጠብደል የባንክ ሂሳብ ያውም በዶላር ክበዋል:: ቁምጣ ከመግዛት የዘለለ ቅሪት ያልነበራቸው ወንበዴዎች ዛሬ ሌብነትና ጉቦ ምስጋና ይግባቸውና የናጠጡ ቱጃሮች ሆነውብናል::

የዋጋ ግሽበትን ለመሰሪ አስገባሪነት በመጠቀም ላይ ያለው የወያኔ መንግስት ህዝቡን እየጋጠ ለባለሚሎቹና ካድሬዎቹ መበልፀጊያነት አውሎታል:: እንደወትሮው ነጋዴዎች የዋጋ ንረት ተጠቃሚዎች ነበሩ:: አሁን ግን የደሞዝተኛው: የጡረተኛው: በወዙ-አዳሪው ያህል ባይሆንም ነጋዴውም የችግሩ ሰላባ ሆኗል:: ዋጋ በጨመረ ቁጥር በውድ እየገዛ ለደንበኞቹ ደግሞ የራሱን ትርፍና የመንግስት ቀረጥን አክሎበት ሊሸጥ ሲሞክር አንደኛም ሸማቹ ከአቅሙ በላይ ይሆንበታልና ንግዱ ይቀዘቅዝበታል አልያም ኪሳራ ገብቶ እራሱንና ቤተሰቡን እንደሌላው ለችግር አለንጋ ያጋልጣል:: በንግዱ ዘርፍ ትርፍና ንዋይ ለመሰብሰብ ጉቦ የግድ ሆኗል::

ጉቦ ብዙ መልክና ውስብስብ ቴክኒክን ተጎናጽፋለች:: ጉቦ በማንኛውም ወቅት አውዳሚ ሚና ቢኖራትም የዋጋ ግሽበት በተንሰራፋበት አገር ግን የአየር-ባየር ንግድን ማከናወኛ ቁልፍ መሳሪያ ትሆናለች:: ዋጋ ሲንር ሁሉን ነገር ትቶ ብድር ወደሚገኝበት ቦታና አበዳሪ ደጅ ማምራት ብልህነት ይመስላል:: በተጻጻሪው ገንዘብ ማበደር ትርፉ ችግርና ቅሪትን ማሟጠጥ ነው:: ጠቀም ያለ ብድር ደግሞ ሊገኝ የሚቻለው ደግሞ ከባንኮችና ከቱጃሮች ነው:: በባንክ ገንዘብ ማስቀመጥ እርግጥም ግብዝነት ነው:: ለምሳሌነት እንኳን ብንወስድ አንድ ግለሰብ ገንዘቡን ባንክ ውስጥ በቁጠባ ሂሳብ ለአንድ አመት ቢያስቀምጥ በአመቱ መጨረሻ 3 በመቶ ወለድ ያገኝበታል:: በዚህ አንድ አመት ብቻ የብር የመግዛት አቅም ከ45 በመቶ በላይ በመውደቁ የተነሳ ከፍተኛ ኪሳራን አስከትሏል:: እያንዳንዱ ገንዘቡን ባንክ ያስቀመጠ ግለሰብ ስለ አድራጎቱ ወለድ ሊያገኝ ሲገባው ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከ42 በመቶ በላይ ከማታወላዳ ጥሪቱ ላይ ኪሳራ ይደርስበታል:: ይህንን ለመከላከል አላቂ ባልሆኑ እቃዎች ላይ ወይም ደግሞ በዶላር ጥሪትን ማስቀመጥ ብዙዎች የዋጋ ግሽበት ያሰቃያቸው ህዝቦች ተመራጭ መንገድ ነው:: በየቀኑ የመግዛት አቅሙን የሚያጣው የኢትዮጵያ ብር አይደለም ሌሎች ህዝቦች ኢትዮጵያውያንም ለመቀበል ፍላጎት የላቸውም:: በመሆኑም ብር ተቀባይ አጥታ የዚንባቡዌ ዶላርን ዕጣ ፈንታ ደርሶባት ህጋዊ ገንዘብነቱ ያከትምለታል::

ይህን አደጋ ለመከላከል ቢረዳም የንዋይ ማግበስበሻነት ዋንኛው መንገድ ግን ከባንኮች በተለያዩ ምክንያቶች መበደርና ማገላበጥ ላይ ነው:: ከባንኮች ያለበቂ ማስያዣ መበደር የሚያስችል የስልጣንም ሆነ የጉቦ ሰንሰለት የፈጠሩ ጥቂት ግለሰቦች በመሬትና ህንጻ ንግድ ከፍተኛ ገንዘብ እያካበቱ ይገኛሉ:: ሌላው መንገድና ስደተኛው ኢትዮጵያዊ የሚዶግመው የሚመስለው መንገድ ደግሞ የዶላር ጥቁር ገበያ ነው:: ብር ከባንኮች ተበድረው ወደ ዶላር መንዝረው የመግዛት አቅሙ በየቀኑ እየረከሰ ያለን ብር ማምለጫ ብሎም ትልቅ ትርፍ ማከማቻ ስልት ሆኗል:: ኢኮኖሚው ካሉበት ውስብስብ ችግሮች አንጻር የብር የምንዛሪ መጠንም እያሽቆለቆለ መሄዱ አይቀሬ ነውና እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች በወሮበላው የወያኔ ባለስልጣኖች ተባባሪነት ቁማራቸውን አዘጋጅተው አረንጓዴ መብራታቸውን በመጠባበቅ ላይ ናቸው::

የተወሳሰበው ኑሮዋችንንና ኢኮኖሚያችን ምን ያህል እያሰቃየን እንደሆነ ለመገንዘብ የስራአጥነትና የዋጋ ግሽበት ቀንበራችንን መመዘን ይገባል:: የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ እንዲሉ ስራ አጥነት በተንሰራፋበት ኢትዮጵያ: ኑሮ ከመነሻውም ከእጅ ወደ አፍ እና ድህነት በተንሰራፋባት ኢትዮጵያ: ከምጽዋት ያልተላቀቀች ኢትዮጵያ: ጉቦና ወሮበላነት በነገሰባት ሃገራችን የዋጋ ግሽበት ጭርሱን ከማያወላዳ መቀመቅ ውስጥ ከቶናል:: ትምህርታቸውን አጠናቀው በአፍላ የወጣትነት ዘመናቸው ስራ አጥነት ህይወታቸው የሆኑ ኢትዮጵያውያን በጣም ከፍተኛ ነው:: የከተሞችን ስራአጥነት ላይ ያተኮረ አንድ ጥናት እንዳመለከተው የተማረና ስራ ፍለጋ ላይ ካሉት ወጣት ዜጎቻችን መካከል ከ51 በመቶ በላይ ስራ አጦች ናቸው:: ዘመድ ወይ ካድሬ ባለስልጣን ካሌለው በቀር ለስራ ብቁነትና ፍላጎት ብቻ ስራን አያስገኝም:: ኢኮኖሚያችን በእርግጥም ካደገ ይህንን ያህል የተማረ ወጣት ስራ አጥነት እንዴት ሊንሰራፋ ይችላል?

በሌላ መልኩ ደግሞ በከተሞችም ይሁን በግብርናው ዘርፍ ለመመዘን አዳጋች ነገር ግን ከፍተኛ የስራአጥነት ችግር እንዳለ መገንዘብ ይኖርብናል:: የዋጋ ግሽበትና ስራ አጥነት ሲዳመሩ ውጤታቸው መርዛማ ቶኒክ ነው:: በእርግጥም ዋጋ በጨመረ ቁጥር ገቢያችንን ስለሚሸረሽረው ረከስ ወዳለው ግብይት ማድረጋችን ግድ ነው:: ሆኖም ግን ብዙዎቻችን ከአብዛኛው የሸቀጥና አገልግሎት ግብይት በዋጋ ንረት ተባረናል:: እናም ነጋዴዎች የመነመነ ንግዳቸው ጨርሶ እንዳይዘጋ በኪሳራም ቢሆን ዋጋ ላለመጨመር ቢሞክሩ አያስገርምም:: ችግራችን የጋራ ነው:: ታድያ የድረሱልን ጩኸታችን እንደጥሩምባ ጆሮን ቢያነጡዝ ከችግር የመነጨ ነውና ከሰሚም ርህራሄን አይነፈገውም ይመስለኛል::

ከጩኸት ሁሉ አብጋኝ ግን እኔ ልቅደም ብሎ ወግድ እያለ ከተማውን የሚያምሰው አይነቱ ነው:: በራሳቸው ጥላ የሚበረግጉ አሳማዎች ድሃው የእለት ጉርሱን ለማግኘት እንዳይሯሯጥ ራሳቸውን ኮፍሰው: መንገዳችንን ዘግተው: ጥሩምባና እምቢልታ አስጎሽመው: የፖሊስ መዓት በመንገዱ አፍሰው ያስገላምጡናል: ያስመናጭቁናል:: ይህኛው የጩኸት አባዜ የእብድነት መንደርደሪያ ወፈፌነት ይሰኛል:: በፍጥነት ወደ ለየለት እብድነትና ነቀርሳነት ለመሸጋገር ብዙም አይሳነውም:: በተለይም በሽታው የተጠናወታቸው ሰው መሰል ወሮበላ አሳማዎች መሆናቸውን ለተረዳ ችግሩ በጠበል የሚፈወስ አባዜ አለመሆኑን ይገነዘባል:: የህይወት ስሯ እንደተናጋባት ጥጃ ወያኔም ስሩ ተናግቷል:: ይህ አይነቱ ነቀርሳ ደግሞ ተደጋግሞ እንደታየው መቃብር ሳያደርስ አይሽርም::

## የግንቦት7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶር ብርሃኑ ነጋ የአውሮፓ ጉብኝታቸውን እንደቀጠሉ ነው ::

(ከገጽ 1 የዞረ)

በዚህም የተነሳ ይህንን የውርደት ኑሮ ተቀብለው ለመኖር ያልፈቀዱ : ለነጻነታቸውና ለብሄራዊ ጥቅማቸው መከበር የሚያስፈልገውን መዋዕትነት ሁሉ ከፍለው ነፃ ለመውጣት ሰፊ ራዕይ ሰንቀው የተደራጁ ሃይሎች ከዚያ ከምርጫ 97 አብዮት የተወለዱ በመሆናቸው ከአሁን በኋላ እንደከዚህ በፊቱ የታሰረ ሰው እንድታስፈቱልን ወይም የስልጣን ዕድሜ ለማራዘም ሲባል በዜጎቻችን ላይ የሚፈጸመውን ግዲያና ሰቆቃ ለማስቆም እንድትተባበሩን አቤቱታ ለማቅረብ ሲባል የሥራ ጊዜያችሁን የሚያባክን አጋጣሚ ይዘንባችሁ እንደማንመጣ ለማሳሰብ እንወዳለን በማለት የንቅናቄያቸውን አቋም አስረድተዋል :: ካነጋገሩዋቸው የአውሮጳ ባለስጣናት ውስጥ በምርጫ 97 ውጤት መጭበርበር ምክንያት ለተነሳው ውዝግብ ሰላማዊ መፍትሄ ለመሻት ዶ/ር ብርሃኑ ቅንጅትን ወክለው የተጫወቱትን ሚና እስከዛሬ የሚያስታውሱ ባለስልጣን የነበሩበት ሲሆን እኚሁ ባለስልጣን መለስ ዜናዊ በእብሪት ተወጥሮ በወሰደው እርምጃ የኋላ ኋላ ዋጋ መክፈሉ አይቀሬ እንደነበር ብዙዎች ባለሥልጣናት በወቅቱ ገምተው እንደነበር አውስተው የተበላሸው የጆርጅ ቡሽ የውጭ ፖሊሲና በሱማሊያ የተከሰተው ሁኔታ በወቅቱ መወሰድ የነበረበትን እርምጃ እንዳወሳሰበው ሳይደብቁ ተናግረዋል ::

በውይይቱ ወቅት በምዕራቡ አለም አእምሮ ውስጥ ስለሚንገዋለለው የአክራሪ እስልምና ስጋት: በሱዳንና በሱማሌ ውስጥ ሰላለው የፀጥታ ችግርና ይህም ወደ ባሰ አለመረጋጋት እያመራ ያለውን የኢትዮጵያን ጉዳይ ታክሎበት በምስራቅ አፍሪካ ቀንድ ከዚያም በአካባቢውና ከአካባቢው ውጭ ባለው ሰላምና መረጋጋት ላይ ሊኖረው የሚችለውን አንድምታ ተነስቶ በሚያመረቃ ጉዳይ መግባባት ተደርሶበታል:: ከ2 አመታት በፊት በሼክ ሸሪፍ የሚመራውን ለዘብተኛ የሱማሌ ጊዜያዊ መንግሥት ከሥልጣን ለማባረር የመለስ ዜናዊ ቡድን ለምን ምዕራባዊያን በተለይም ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካንን በተሳሳተ መረጃ በሱማሌ ላካሄደው ወረራ አጋር አድርጎ እንዳስገባና በርካታ ሱማሌዎች ከተገደሉ ከተሰደዱና በሰብዓዊነት ላይ ያነፃፀሩ ሰቆቃዎች ከተፈጸሙባቸው ቦኋላ እራሳቸው ሼክ ሸሪፊ እንዲመለሱ ቢደርግም እንኳ በዋንኛነት ወረራው በፈጠረው ከፍተኛ የአክራሪነት ስሜት ምክንያት ከወረራው በፊት የነበረውን እነስተኛ መረጋጋት መልሶ ለማምጣት ምን ያህል እንዳስቸገረ በመግለጽ መለስ ዜናዊ ስልጣን ላይ እንዲቆይ ከተፈቀደለት ከዚይ የከፋ እደጋ ለአገራችንና ለአካባቢያችን እንደሚተርፍ ተጨባጭ ማስረጃዎችን በማመላከትና አየተፈጠሩ ያሉ የስጋት ምልክቶችን ዋቢ በማድረግ አስረድተዋል ::

በመጨረሻም ግንቦት 7 ንቅናቄን ጨምሮ አገራቸውን ከመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ትግል የጀመሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ምንም ዓይነት ድጋፍና ትብብር ከም'ዕራቡ አገር ሳያስፈልጋቸው የተነሱበትን አላማ ከግብ ለማድረስ እንደሚችሉ ያረጋገጡት ዶ/ር ብርሃኑ በዚህ ትግል ውስጥ የተካተቱት ሃይሎች ሁሉ በአገራቸው ውስጥ አሁን ስልጣን ላይ ያለው ሃይል የመጨረሻው አምባገነን ሆኖ ወደታሪክ ትቢያ እንዲወርድ የጋራ ስምምነት አንዳላቸው ገልጸው በቅርቡ ተግባራዊ አንቅስቃሴዎች እንደሚከተሉ አሳውቀዋል:: በዚህ ሂደትም በመጀመሪያ የአገራችን: ቀጥሎም የአካባቢያችንና ከዚያም የምዕራቡ አለም ዘላቂ ጥቅም በአሰተማማኝነ ሁኔታ እንደሚጠበቅ በእርግጠኝነት ገልጸዋል:: ስለዚህም ምንም የሚያሳስባችው ነገር እንደለለ ኢትዮጵያዊያኑ ሊያካሁዱት በተዘጋጁት ሁለገብ ትግል ቁርጠኝነት ድንጋጤ የተሰማቸውን ባለስልጣናት ካሳወቁ ቦኋላ ለተመሳሳይ ተልዕኮ ወደ ቀጣዩ አገር አምርተዋል ::

ዶ/ር ብርሃኑ ባለፈው እርብ ግንቦት 7 ቀን ከስውድን መንግሥት ባለሥልጣናት ጋር ግንቦት 10 ደግሞ ከኖርዌይ ባለሥልጣናት ጋር ተመሳሳይ ውይይት እንዳደረጉ የንቅናቄያችን ውጭ ግንኙነት ክፍል አስታውቆአል ::

## በድርጅቱ ውስጥና ውጭ የተደናገጠው ወያኔ ቀደም ሲል ሥራቸውን የለቀቁ ፖሊሶች ታድነው እንዲያዙ

(ከገጽ 1 የዞረ)

በአሁኑ ጊዜ በፖሊስ ሰራዊት ውስጥ ያለው ሽኩቻ ከመቼውም ጊዜ በላይ እየከፋ መምጣቱን የሚናገሩት የውስጥ ምንጮች፣ ሽኩቻው አንዳንድ ጊዜ ወደ ብሄር ግጭት እንደሚለወጥም ተናግረዋል። በተለይ በትምህርታቸው ዲፕሎማና ሰርተፊኬት የያዙ የፖሊስ አባላት፣ በዘራቸው ምክንያት ለአመራርነት ቦታ እንደማይታጩ የሚታወቅ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ በአመራር ላይ የሚገኙት የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያልጨረሱ የአንድ ብሄር ተዋላጆች ብቻ መሆናቸውን የወያኔ መሪዎች በተለያዩ ጊዜዎች መናገራቸው ይታወቃል።

በርካታ የፖሊስ አባላት በማታ ትምህርት ፕሮግራም ራሳቸውን ከለወጡ በሁዋላ፣ የውስጥ እደገት በማጣታቸው እንደሚለቁ የፖሊስ አባላቱ የሚናገሩት ቢሆንም፣ በቅርብ ጊዜ እየታየ ያለው የፖሊሶች ኩብለላ ግን ከእስካሁኑ ሁሉ የተለየ መሆኑን ምንጮቻችን አክለዋል።

## መለስ ዜናዊ አፊሪካ ኮንፊደንሻል ለተባለ ጋዜጣ በሰጠው ቃለመጠይቅ የግንቦት 7 ንቅናቄ ራስምታት እንደፈጠረበት አመነ

(ከገጽ 1 የዞረ)

ከጋዜጣው ጋር ባደረገው ቃለምልልስ መለስ በቅርብ ጊዜ የከፍተኛ አመራሮች ሹም ሽር እንደሚኖር ተናግሮአል። በፍርሀት እና በጭንቀት የሚይዘውን እና የሚጨብጠው ያጣው ወያኔ ከቀን ወደ ቀን የእኔ የሚላቸው ታማኞቹ እየከዱት መምጣታቸው እና በአካል አብረውት ያሉትም ቢሆኑ ልባቸው በመኮብለሉ ጭንቀቱ እንደተባባሰበት እና የሹም ሽር ጊዜውን እንዳቃረበው ታውቋል። የወያኔ ውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ከሰሞኑ በአሜሪካ : በፈረንሳይ ; በጣሊያንና በጀርመን የሚገኙ አምባሳደሮች ወደ አገር ቤት ያስጠራ ሲሆን የሹም ሽሩ ሰለባ ይሁኑ ወይም ተቀባይነቱ እየቀነሰ በመምጣቱ ከቅሌት ሊወጣ የሚችልበትን ዜዴ በጋራ ለመዘየድ ለጊዜው የታወቀ ነገር የለም ::

ከአመታት በፊት በኦህዴድ አባለት እና አመራሮች የተበሳጨው መለስ "ከሜዳ አንስተን ሚኒስትር አደረግናችሁ። እናንተ ግን ውለታ አታውቁም። ልባችሁ ከኛ ጋር አይደለም፤ ሁላችሁም ብትፋቁ አነጎች ናቹሁ።" ብሎ እንዳንኳሰሳቸው የሚታወስ ሲሆን ከአሁን ቦኋላ የወቅቱ ጥቃት ዕላማ የሆኑትን የብአዴን አባላት "ሁላችሁም ብትፋቁ ግንቦት ሰባት ናችሁ " በማለት የጀመረውን ጥቃት እንደሚያፏፉም ይጠበቃል ።

## በአማራው ክልል በርካታ ሰዎች የግንቦት 7 አባላት ናችሁ እየተባሉ በመታሰር ላይ ናቸው

(ከገጽ 1 የዞረ)

እነዚህ ዶክመንቶች ከዚህ አስቀድሞ ተዘጋጅተው የተቀመጡ ቢሆኑም አሁን ለሚካሄደው ግምገማ መጠቀም ለምን እንዳስፈለገ ሪፖርተራችን ላቀረበላቸው ጥያቄ በወያኔ ክፍፍል ወቅት የነ ስዬ አብረሃን ቡድን ትደግፋለህ በሚል ከተመነጠሩ ነባር የወያኔ አባላት መካከል፤ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ አንድ ሰው ሁኔታውን እንዲህ በማለት ተችተዋል፡- "ግምገማ ከምትለው የስድብ መድረክ በለው። ይሄ በግምገማ ሰበብ የማይፈልጓቸውን ሰዎች መምታት የተለመደ ነው። ግምገማ ይደረግ ይባላል። አባሉ በሞላ አገር አማን ነው ብሎ ለግምገማ ይሰበሰባል። ለግምገማ በሚቀርቡ ሰዎች ላይ የሚናገሩ አስቀድመው የተዘጋጁ ተሳዳቢ ካድሬዎች ይዘጋጃሉ። ከዚያም ሊመነጥሩአቸው ያሰቡአቸው ሰዎች ላይ የስድብ ናዳ ይወርዳል። አንድ ስሙን እንኳ አስተካክሎ መጻፍ የማይችል ካድሬ እየተነሳ "እገሌ ጠባብነት ያጠቃዋል" እያለ ይዘልፋል። የሚገመገመው አማራ ከሆነ ደግሞ እገሌ ትምክህተኛ ነው እያለ በል የተባለውን ትርጉሙን ሳያውቀው እንዲናገር ይደረጋል። ትምክህተኛ፣ ሙሰኛ ተብለህ ብዙ ገንዘብ ከመንግስት ካዝና የሰረቅህ ተደርገህ ትቀርባለህ። ራስህን ከተከላከልክ ደግሞ ግለ ሂስ አልዋጥክም ትባላለህ። ሰነዶች ለምን ይዘጋጃሉ ላልከው አንድ ምክንያት ነው ያለው። ግምገማ አለ በተባለ ቁጥር መለስ አንድ ወረቀት ያዘጋጅና እርሱ ከሁሉም የላቀ መሆኑን አጋጣሚውን ተጠቅሞ የሚያረጋግጥበት ስለሆነ እንጂ ለግምገማው ፋይዳ ስላላቸው አይደለም።

ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላም እንዲሁ በፓርቲው ውስጥ ስለ ዴሞክራሲ ስለ መልካም አስተዳደር ተጨንቀው ጥያቄ አንስተው የነበሩ ሰዎች ከዚያ በኋላ በተደረጉ ግምገማዎች ተባረዋል። ያን ጊዜም እንዲሁ "ዴሞክራሲና ዴሞክራሲያዊ አንድነት" የሚል በመለስ የተጻፈ አንድ ጽሁፍ ቀርቦ ነበር። ከግምገማዎቹ በኋላ በርካታ ካድሬዎች፣ ፖሊሶችና የመከላከያ ሰራዊት አባላት ከስራቸው ተባረዋል። አሁን ተሞከረ በተባለው መፈንቅለ መንግስት ሙከራ ምክንያት እንደውም ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናትም የዚሁ ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ እጠራጠራለሁ። በተለይ የሰሞኑ የሪፖርተር የማሻሻያና ሹም ሽር ይደረግ እሮሮ ሊመጣ ያለውን ነገር አመላካች ነው" በማለት ሃሳባቸውን ደምድመዋል።

ዘጋቢያችን ያነጋገረው ሌላ አንድ የነጻው ፕሬስ ጋዜጠኛም፥ ስለሪፖርተሩ የሰሞኑ እሮሮ ተመሳሳይ አስተያየት የሰጠ ሲሆን፣ እንዲህ ሲል አክሎበታል፡- "የወያኔ የአንድ ወቅት የቤት ልጅ እና የዛሬው ስደተኛ ተስፋዬ ገ/አብ በማስታወሻው ስለ አማረ የሚያውቀውን ነግሮናል። 'ወያኔ በምርጫም ይሁን በሃይል ከስልጣን የሚወገድ ከሆነ አማረ የመጀመሪያው ጫካ ገቢ ይሆናል' ያለውን መዘንጋት የሚያስፈልግ አይመስለኝም። ሰሞኑን የተከሰተው ነገር እጅግ ስላሰጋው አንድ ጊዜ ስለሰላማዊ ትግል፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ስለ አንድነት፣ አሁን ደግሞ ሹም ሽር ይደረግ ሲል እየተሰማ ነው። ሰውየው ቤተኛ መሆኑን አትዘንጋ። ሰዎቹ ሊወስዱ የፈለጉትን እርምጃ በእርሱ በኩል ነው አስቀድመው ይፋ የሚያደርጉት" በማለት አስተያየቱን ቋጭቷል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org